**ከበድር ኢንተርናሽናል የኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ማህበር፣ ከሰሜን አሜሪካ፣ ከአዉሮፓ፣ ከመካከለኛው ምስራቅና ከኤሲያ የኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ማህበራት**

**ለጠቅላይ ሚኒስትር ክቡር መለስ ዜናዊ የኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ጉዳይ በማስመልከት የቀረቡ ጥያቄዎች**

*ሚያዚያ 1999 /April 2007*



*በአላህ ስም እጅግ አዛኝና ርህሩህ በሆነው*

# መግቢያ

ሀገራችን በእስልምና ልዩ ቦታ አላት። የመጀመሪያዎቹ የእስልምና የታሪክ ምዕራፎች ሀገራችንን የእውነትና የፍትህ ሀገር፣ እምነቱ በአስተዳደር ደረጃ እዉቅና በመጀመሪያ ያገኘበትና ንጉሷም መልዕክቱን የተቀበለባት ሀገር በማለት ይዘክሯታል። ስቃይና መከራ አልቻላቸው ብለው መጠለያ ፈልገው ለተሰደዱ ሙስሊሞች በሯን ከፍታ፣ እጇን ዘርግታ ከመቀበሏና በጥሩ ሁኔታም ከማስተናገዷ ጋር እምነቱን የተቀበሉ ዜጎቿ ከሌሎች ወገኖቻቸው ጋር በመከባበርና በመቻቻል በሰላም አብረው የኖሩባት ሀገር በማለት ያወሷታል።

ወደሀገሪቱ ከገቡ የአይሁድና ክርስትና ኃይማኖቶች፣ እንደዚሁም ከሀገሪቱ ነባር እምነቶች በተጨማሪ ሀገራችን በእስልምና አሸበረቀች፣ ከአጎራባች ሥልጣኔዎች ጋር አብሮ መኖር የምትችል መሆኗንም አስመሰከረች። ክስተቱ ቀጣዩን የኢትዮጵያንና እስላም ግንኙነት እንደዚሁም የኢትዮጵያን የዉስጥ ታሪክ በጉልህ አቅጣጫ አስያዘ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮም “ኢትዮጵያ እና እስላም” ሳይሆን “ኢትዮ-እስላም” /*Ethiopian Islam*/ የራሱ ባህሪይና ገፅታ ተላብሶ በሀገራችን ተከሰተ፣ አደገ፣ አበበም። እምነቱም በ1435 ዓመታት በሀገራችን ቆይታው ታሪካዊና ባህላዊ ቅርሳችን ሊሆን በቃ።

በዘመነ አክሱም መገባደጃ ላይ እዉን ለመሆን የበቃዉ የኢትዮጵያ ገፅታ አድጎ ወይንም እንዳለ ተጠብቆ ሊቀጥል አልቻለም። በቀጣይ የተከሰቱ የአገዛዝ ስርዓቶች በተለይም ሰለሞናዊው ሥርዐ-መንግስት /1260 - 1966/ የአክሱምን ቤተ መንግስት ታሪክ በተጻረረ መልኩ በስፋት ተንቀሳቅሷል። በመካከለኛው ዘመን በሀገራችን ሰፊ ክፍል እውን ከነበሩት እስላማዊ ሥርዓቶችና ስልጣኔዎች ጋር የተደረገው ወታደራዊ ግብግብ ከ7ኛው እስከ 13ኛው ክ/ዘመን በነበረን አኩሪ ታሪካችን ላይ መፈንቅለ ሥርዓት የተካሄደ መሆኑን ያመላክታል። እስላም ጠላት ተደርጓል። ሙስሊሞችም እንደ ባዕድ ታይተዋል። ቢሆንም የመንግስትን ታሪክ ከህዝብ ታሪክ ለይተን ማየት ያለብን በመሆኑ በኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች መካከል የከፋ የግንኙነት መሻከር ነበር ብለን አናምንም። በየትኛዉም መለኪያ ግን ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ለዘመናት ተንቀው፣ ለባህላዊ ተቋማቸው ጥበቃ ሳይደረግ፣ በእምነታችው ምክንያት ብቻ ለእንግልትና ለስደት ተዳርገው ኖረዋል። በሀገሪቱ የትምህርት፣ የማህበራዊና የፖለቲካዊ ህይዎት ተሳታፊ ሳይሆኑ የኖሩ ለመሆናቸው ታሪካዊ ዋቢን ማጣቀስ አያስፈልገውም። የዚህ የተዛባ ግንኙነት አሻራም እነሆ ለዘመኑ ኢትዮጵያዊ ሙስሊም ተርፎ ጠንካራ ተቋማዊ መሰረት በማጣት በመንታ መንገድ ላይ እየዋለለ ይገኛል።

አሁን ያለው መንግስት በታሪክ የተፈጠሩ፣ የተዛቡና ሚዛናዊ ያልሆኑ ግንኙነቶችን ለማረም ፈቃደኛ ሆኖ የተነሳ መንግስት በመሆኑ በታሪካችን ካየናቸው መንግስታት የተሻለ ለመሆኑ ጥርጥር የለንም። እንደዋነኛ ምክንያት ከሚሆኑት መካከል የእምነት ነጻነትና እኩልነት በሕገ-መንግስቱ የማያሻማ እውቅና ማግኘቱ አንዱ ነው። ይሁንና በሙስሊም ዜጎቹ ላይ የሚከተለው የፓሊሲ አቅጣጫና አፈጻጸም ወጥነት የሌለው ሆኖ ይታያል። ይህም ወደ መመጣጠን አቅጣጫ /*Equilibrium*/ በመጓዝ ላይ ያለውን የኃይማኖቶችና የህዝቦች

ግንኙነት ወደ ኋላ እንዳይመልሰው እንሰጋለን። ከዚህም በተጨማሪ በታሪካችን ስለተፈፀሙም ሆኑ በአሁኑ ወቅት በሙስሊሞች ላይ ሰለሚደረጉ በርካታ ማነቆዎችና ሰለሚፈፀሙ ውጣ ዉረዶች በቂ ግንዛቤ ለሌለው ኢትዮጵያዊው ሙስሊም ማህበረሰብ ከእስላም አኳያ መንግስት የሚከተለውን መርህ በጎነት ለማሰረዳት አስቸጋሪ የሆነበት ሁኔታን እናያለን።

ሙስሊሙ ኢትዮጵያዊ - በሀገርም ዉስጥ ሆነ በውጭ ያለው - በርካታ ጥያቄዎችን ያነሳል። መንግስት በሙስሊሙ ህብረተሰብ ዘንድ ቅንጣት ያክል ተአመኔታና ተወካይነት የሌለው፣ ለህብረተሰቡም ምንም አይነት ግልጋሎት ሊሰጥ ያልቻለው የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት (መጅሊስ) አስተዳደር ይለወጥ ዘንድ ለቀረበለት ጥያቄ ምላሽ ባለመስጠቱ የዜግነትና የሙስሊምነት መብታችንን ተጋፍቷል፤ በነፃ ማህበራትን የማቋቋም መብታችንን በቢሮክራሲያዊ ማነቆ አዳክሟል፤ በተለያዩ የህይዎት ዘርፎች የመወዳደር አቅማችንን አሳጥቶናል፤ በማንነታችን እና በእምነታችን ላይ በተሰነዘሩና እየተሰነዘሩም ላሉ ወንጀሎች ትኩረት ሰጥቶ አመርቂ ምላሽ ሊሰጥ ባለመቻሉ ፍትህን ነፍጎናል፤ ሕገ-መንግስቱ የሰጠው የኃይማኖቶች አኩልነት እስላም እና ሙስሊሞች ላይ ሲደርስ ተፈጻሚነትን አጥቶአል የሚሉት በዋነኛነት የሚጠቀሱ ናቸው። እነዚህና ሌሎችም ተመሳሳይ ከሕገ-መንግስታዊ ማዕቀፍ የማይወጡ እንደዚሁም የሀገሪቱን ሴኩላር ሥርዓትና በማደግ ላይ ያለዉን የድሞክራሲ ሂደት ከግንዛቤ ያስገቡ ጥያቄዎቻችን በዉይይት ሊፈቱ እንደሚችሉ በማመን ከክቡርነትዎ ጋር በመመካከር በጋራ መፍትሄን ለመሻት ውቅያኖስ አቋርጠን ወደ ትውልድ ሀገራችን መጥተናል።

ጥያቄዎቻችን የድርድር ወይም የወቀሳ መንፈስ የላቸውም። አቤቱታ ሆነው የበርካታ ሙስሊም ዜጎችዎን ውስጣዊ መንፈስ በግልፅ እንዲያነቡ፣ ያላቸውንም ብሶት እንዲረዱ ያስችላሉ ብለን ያመንባቸው ነጥቦችና መነሻ ሃሳቦች ናቸው። በሀገራችንና በህዝባችን ላይ ያሉ ችግሮችን አብረን በጋራ ለመፍታት ካለን ዝግጁነትና ለዚህም በመንግስት በኩል ለማግኘት ከቻልነው መልካም ፈቃደኝነት የመነጩም ናቸው። ለሙስሊሙ ህብረተሰብ ለትምህረት፣ ለፍትህ፣ ለእኩልነት፣ ለልማት፣ ለባህላዊና መንፈሳዊ እድገት መዳረሻ /Access/ በመፍጠር በኩል ቁልፍ ሚና የሚጫዎቱ ሲሆኑ በውይይታችን መንግስትንም ህዝብንም ሀገርንም የሚገነባ መፍትሄ ላይ ለመድረስ እንችላለን የሚል እምነት አለን። ሊያነጋግሩን ፈቃድዎ በመሆኑ በኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ስም ጥልቅ ምስጋናችንን እያቀረብን ጉብኝታችንም ቀጣይና ቋሚ ፍሬ እንዲያስገኝ እንመኛለን።

በዚህ አጋጣሚ ቅን አሳቢ ለሆኑት አምባሳደር ሳሙኤል አሰፋ ለዚህ ጉብኝት መሳካት ላበረከቱት አስተዋፅዖ ያለንን አክብሮትና ምስጋና ልንገልፅ እንወዳለን።





# ለክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የቀረቡ ጥያቄዎችና የዉይይት መነሻ ሀሳቦች

ከላይ በመግቢያችን ጠቀስ አድርገን እንዳለፍነው ሙስሊሙ ህበረተሰብ የሚያነሳቸው በርካታ ጥያቄዎች አሉት። እነዚህ ጥያቄዎች የሀገሪቱ ሕገ-መንግስት ለዜጎቹ የሰጠውን መብትና የኃይማኖት እኩልነት እንደዚሁም ሀገሪቱ የምትከተለውን ሴኩላር አስተዳደር መሰረት ያደረጉ ያለችበትንም የዲሞክራሲ ጎዳና ያገናዘቡ ናቸው። የተከበሩ ጠቅላይ ሚኒስትር ይዘን ለመጣናቸው ጥያቄዎቻችን ትኩረት ሰጥተው ተገቢ ምላሽ እንደሚሰጡን በመተማመን እንደሚከተለው እናቀርባለን::

## 1. የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት /መጅሊስ/ በአዲስ መልክ ይዋቀር፤ ሙስሊሙ ያመነባቸውና የወከላቸው አካላትም በአመራር ላይ ይቀመጡ፤

የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ኦፊሴላዊ የኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ወካይ ድርጅት እንደመሆኑ አወቃቀሩን በተመለከተም ሆነ ድርጅቱን በሐላፊነት በሚመሩ ሰዎች ላይ ህዝበ ሙስሊሙ ከፍተኛ ቅሬታ አለው።

መጅሊሱ የኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ለረጅም ጊዜ የታገሉለትና የደከሙበት፣ ከ1966 ህዝባዊ ድሎች መካከል አንዱ ሆኖ በመጋቢት 20፣ 1968 ተቋቋመ። ምንም እንኳን መሰረታዊ ግቦችን አንግቦ ቢነሳም ሙስሊሙ የነበረበትን መጠነ ሰፊና ዉስብስብ ችግሮች ለመፍታት የሚያስችል ድርጅታዊም ሆነ ማቴሪያላዊ ብቃት ግን አልነበረዉም። ይኸው ከሶስት አስርተ አመታት በኋላምና በዘመነ ዲሞክራሲም ይህ ነው የማይባል የአደረጃጀትና የአሰራር ለውጥ ሊያደርግና ብቃቱንም ወቅቱ በሚጠይቀው መልክ ማሳደግ አልቻለም። ይህም በመሆኑ በአሁኑ ሰዓት ሙስሊሙን የሚፈታተኑ፤ የዚህም (በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ) ዉጤት የሆኑና በሀገሪቱ እድገትና ሰላም ላይ ተፅዕኖ እያደረጉ ያሉ መሰረታዊ ችግሮችን ሊፈታ አልቻለም።

በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ ሙስሊሙ ችግሬን ያዉቁልኛል፤ ይወክሉኛል፤ ለእምነቱ መከበርና ለእኩልነት ታግለው ያታግሉኛል፤ ለልማት፣ ለፍትህ እና ብልፅግና ያበቁኛል የሚላቸውን አካላት በሐላፊነት ቦታ ለማስቀመጥ የሚችልበት እድል እስካሁን አላገኘም። በዚህም ምክንያት የሙስሊሙ ችግሮች እየተባባሱና እየተወሳሰቡ ይገኛሉ። በኃይማኖትም ሆነ በአለማዊ እዉቀት ብሎም በሙያዊ ብቃት እጅግ ያነሰ ደረጃ ያላቸው ግለሰቦች ስለምን በዚህ ድርጅት ወሳኝ የአመራር ቦታ ላይ እንደተቀመጡ ህዝቡ የሚያውቀው ጉዳይ አልሆነም።

ወቅቱ በሚጠይቀው መልክ የተቋቋመና የሙስሊሙንም ተአመኔታ ያገኘ መሪ ድርጅት አለመኖሩ በሙስሊሙም ሆነ በሀገሪቱ እድገትና ሰላም ላይ እያስከተለ ያለው ጉዳት ቀላል አይደለም። መጅሊሱ የሙስሊሙ ብቸኛ ተወካይ ከመሆኑ አንፃር የመሪነትን ሚና በመጫዎት ለሙስሊሙ ጥያቄዎች መልስ ለማስገኘት መጣር፤ ሙስሊሞችም በሀገራቸው ነባራዊ ሁኔታ እንደዚሁም ልማትና እድገት ላይ አመርቂ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ጥረት

ማድረግ፣ ሀገራችን ከጎረቤትና ሙስሊም ሀገሮች ጋር ያላትን ትሥሥር ለማጠናከርና ከሌሎች ኢትዮጵያዊያን ጋር በመቻቻልና በመከባበር ለመኖር የበኩሉን አስተዋፅዖ ማድረግ ተቀዳሚ ተግባሩ ነበር ብለን እናምናለን። የእስካሁን ክንዋኔዎቹ በግልፅ የሚያመላክቱት ግን የዚህን ተቃራኒ ነው።

በብዙ አጋጣሚዎች የሙስሊሙን ጉዳይ ወደ ጎን በመተው የዉጭ ተመልካች ከመሆን ባሻገር የሙስሊሙ ጉዳይ ያሳስበናል ያሉ ሀገርና ወገን ወዳድ ሙስሊሞችን እንደ ጠላት በመፈረጅ በነሱ ላይ ቀዳሚ ዘማች ሆኖ ታይቷል። ሙስሊሙን ህብረተሰብ አንድ ከማድረግ ይልቅ በመከፋፈል አንዱን ዜጋ ህጋዊ ሌላውን ህገ-ወጥ እያለ በመፈረጅና አላስፈላጊም ስም በመስጠት ስራ ላይ በማዘውተሩ ከሙስሊሙ ህብረተሰብ አልፎ ለሀገሪቱ ሰላምና አንድነት ጠንቅ፣ ለምታደርገውም የልማት እንቅስቃሴ እንቅፋት እየሆነ ይገኛል። ጉዳዩ ከሚመለከተው የሚኒስቴር መስሪያ ቤት ፈቃድን አገኝተው ከሚንቀሳቀሱ ሕጋዊ ድርጅቶች ጋር በሚፈጥረው አሰጥ አገባም አላስፈላጊ ሁከት እየቀሰቀሰ ይገኛል። ጥቅም የለሽ በሆነ የቲዎሎጂ ፀጉር ስንጠቃ ውስጥ በመግባት ህብረተሰባችንን ማለቂያ በሌለው ትርምስ ውስጥ የሚያስገባ ተቋም ሆኗል። ባለው የችሎታ ማነስና የአሰራር ብልሹነት ዜጎች ይህ ነው ለማይባል እንግልት እና ወጭ እየተዳረጉ ይገኛሉ፣ የሀገራችንና የህዝባችን ስምም እየጠፋ ነው። እንደተቋም ህብረተሰቡን ከማገልገል የግለሰቦች እምነትና ሀሳብ ማራመጃ ሆኗል።

ከላይ ቀንጨብ አድርገን ባወሳናቸውና ሌሎች ተዛማጅነት ባላቸው ድክመቶቹ መጅሊሱ ሀገራችን በልማትና በሰላም ወደፊት እንዳትራመድ እያደረገ ነው። ከዚህም በተጨማሪ በመንግስትና በህዝበ ሙስሊሙ መካከል ጤናማ ግንኙነት እንዳይኖር እያደረገና ከሌላ እምነት ተከታዮች ጋር በሰላምና ተፋቅሮ መኖር የማይቻልበትን ሁኔታም እየፈጠረ ይገኛል።

የኃይማኖት ትምህርትና መሪነት ራሱን የቻለ ሙያ ነው። አሁን ያለው አደረጃጀትና ሙያዊም ብቃት በሌላቸው ግለሰቦች የተያዘው አመራሩ ድርጅቱን ለከፍተኛ ዉድቀት የዳረገና የሚጠበቅበትንም አላማ እንዳያሳካ ማነቆ ሆኗል።

መጅሊሱ መንግስትን በሀገርም ሆነ ከሀገር ውጭ ድጋፍ እያሳጣና የሙስሊሙንም የባህልና የልማት ተሳትፎ ወደኋላ እየጎተተ ይገኛል። ይህም በመሆኑ አስቸኳይና ዘላቂ መፍትሄን ይሻል። ተቋሙ መሠረታዊ የአደረጃጀት ለውጥ ተደርጎበት አመራሩም ለሀገርም ሆነ ለህዝብ ጥቅም በቆሙ ግለሰቦች መተካት ይኖርበታል።

መጅሊስ ማንኛዉም ዘመናዊ ተቋም ከሚደራጅበት ዘመናዊና ቀልጣፋ የአደረጃጀት ዘዴ የተለየ አደረጃጀት የሚጠይቅ አይደለም። አደረጃጀቱ የሙስሊሞችን መሰረታዊ ችግሮች፣ የሀገሪቱን ነባራዊ ሁኔታና የልማት አቅጣጫ ከግምት ባስገባ መልክ መሆን እንዳለበት እናምናለን። በተለይም ተቋሙ የሙስሊሙን ማህበራዊና ልማታዊ ተሳትፎ ማጠናከር በሚችልበት አቅጣጫ ተዋቅሮ ማየት እንመኛለን። የባለሙያዎች ጥልቅ ጥናት አስፈላጊነትም ይታየናል። ከዚህ አንፃር ለቀጣይ ጥናትና ውይይት መሰረት የሚሆኑ በተለያዩ ሙስሊም ምሁራን በግልና በቡድን ተሰርተው የቀረቡ ረቂቆችና ጥናቶችን አሰባስበናል። እነዚህ ረቂቆችና ጥናቶች ተጨማሪ ጥናት ተደርጎባቸው ለሙስሊሙ ህብረተሰብ ቀርቦ ተቀባይነት ያለው የአደረጃጀትና የአሰራር ደንብን ለመቅረፅ ሊጠቅሙ ይችላሉ። በበኩላችን ድርጅቱ በሴክሪታሪያት የሚመራ ሆኖ አስተዳደራዊ ጉዳዮች ለስራው ብቃት ባላቸው ምሁራን የሚሰሩ፣ የኃይማኖት ጉዳዮች ደግሞ በኡለማ (በሐይማኖት ሊቃዉንት) ምክር ቤት ሊወሰን በሚችልበት መልክ ቢቀርብ የተሻለ እንደሚሆን እንመክራለን።





## 2. በሕገ-መንግስቱ የተቀመጡ የዜጎች መብቶችና የኃይማኖት እኩልነት ተፈጻሚ ይሁንልን፤

በሕገ-መንግስቱ የተቀመጡ የዜጎች መብቶች ትርጉም የሚኖራቸው ያለምንም አድሎና ተአቅቦ ተግባር ላይ ሲውሉ፣ ዜጎችም የእነዚህ መብቶች ሙሉ ተጠቃሚ ሲሆኑ ነው። የሕገ-መንግስቱን ድንጋጌዎች መተርጎምና በትክክል ስራ ላይ መዋል መንግስት ሊከታተል ይገባል። የዴሞክራሲያዊ መንግስት አብይ ተግባርም ይኸው ነው ብለን እናምናለን። ሙስሊሞችም በሕገ-መንግስቱ የሰፈሩ መብቶችና ድንጋጌዎች ከተከበሩልን ከዚህ በላይ የምንጠይቀው ነገር አይኖርም። በተጨባጭ የማይታይ የወረቀት መብት ኢትዮጵያዊው ህዝበ ሙስሊሙ ተሰላችቷል። ከዚህ አንፃር ሙስሊሙም ሕገ-መንግስቱ ያረጋገጠው የዜጎች መብቶች ተጠቃሚ ይሆን ዘንድ የሚከተሉትን ጥያቄዎች እናቀርባለን።

### *ሀ. ሙስሊሙ እራሱን በማደራጀት እምነቱን ለመተግበር እንደዚሁም በሀገሩ ልማት በሚፈልገው መጠን እንዳይሳተፍ ያደረጉ ተፅኖዎች ይነሱልን፤*

የመደራጀት መብት መሰረታዊ ሕገ-መንግስታዊ መብት ቢሆንም በዚህ ረገድ ከፍተኛ ክፍተት በሙስሊሙ ህብረተሰብ ዘንድ ይስተዋላል። የወጣት፣ የሴቶችና የምሁራን መንፈሳዊ ማህበራት ሕልውና እንዳይኖራቸው ሆኗል። እነዚህ ወሳኝ የህዝብ ክፍሎች ለህዝባቸውም ሆነ ለሀገራቸው የሚጠቅም ሥራ ማከናወን የሚችሉት መደራጀት ሲችሉና ተቋማዊ መሠረት ሲኖራቸው ነው። የሙስሊሙ እንቅስቃሴ በተገደበ ቁጥር የሀገር ሀብት እንደተጓደለ መታሰብ ይኖርበታል። የተበታተነ የህብረተሰብ ክፍልን ለብሔራዊ መንፈስና አላማ ማዘጋጀትም አዳጋች እንደሚሆን ግልፅ ነው።

ተደራጅቶ እራሱን በልማት በማሳተፍ ኑሮውን የሚያሻሽልበት መንገድ ያጣ ህብረተሰብ ለድህነት ከመጋለጡ በተጨማሪ ለስነ ልቦናዊ አለመረጋጋት ይዳረጋል። መቆጣጠር አስቸጋሪ የሆነ ስንኩል አመለካከት ውስጥ የሚዘፈቁ ኃይላትን በውስጡ ይፈጥራል። ሌላም ሀገሪቱ ልትሸከመው ከማትችለው አዘቅት ዉስጥ ይገባል።

ከሙስሊም ባህል አኳያ የተቀረጹ የፋይናንስ ተቋማትም አስፈላጊ በመሆናቸው ይደራጁ ዘንድ የመንግስትን ድጋፍ እንጠይቃለን። ከወለድ ነጻ የሆኑ ባንኮችና የፋይናንስ ተቋማት ቢቋቋሙ ለሀገሪቱ የገንዘብ አቅም የሚኖራቸው ሚና በቀላሉ የሚገመት አይሆንም። ከሁሉም በላይ ወለድ ውስጥ ላለመግባት ከኢንቨስትመንት የታቀቡ ዜጎችን በልማት ለማሳተፍ አይነተኛ ሚና ይኖራቸዋል። ድህነትን ለመቀነስ የሚደረገውን ጥረትም ያግዛሉ። መንግስት በዚህ ረገድም ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እንዲንቀሳቀስ ወይም በዚህ ዘርፍ ለመስራት የሚፈልጉ ግለሰቦችንም ሆነ ድርጅቶችን እንዲያበረታታ እንጠይቃለን።

### *ለ. ሸሪዓ ፍ/ቤት በሕገ-መንግስቱ የተሰጠውን ሀላፊነት ተግባራዊ በሚያደርግበት መልክ ይቋቋም፤*

የሸሪዓ ፍ/ቤት የሙስሊሙ ታሪካዊ ተቋም ነው። ፍርድ ሸንጎ በቀበሌ ሳይቋቋም፣ የፍትህ ሥርዓት ሳይዘረጋ የቃዲ ቢሮዎች በማህበራዊም ሆነ ከዚያ በላይ ከፍ ባሉ ጉዳዮች ላይ ላቅ ያለ ሚና ነበራቸው። አበጋር ነበሩ።

ይህ የሙስሊሙ መሰረታዊ የሆነ ተቋም ለረጂም ዘመናት ምንም አይነት ተቋማዊ ለውጥ አላደረገም። ይህም በመሆኑ ለህብረተሰቡ የሚጠበቅበትን አገልግሎት ከመስጠት ይልቅ

ችግሮችን እየፈጠረ ይገኛል። ፍትህን ማስፈን በማያስችል መልኩ የተዋቀረ በመሆኑ እና የቁጥጥር "ሜካኒዝም"ም ስለሌለው ሙስሊሙ አላስፈላጊ ለሆነ ወጭ እና እንግልት እንደዚሁም ለፍትህ መጓደል ተዳርጓል። ድሃውን ወገናችንን እያስለቀሰ ነው። የሰጠውንም ውሳኔ የማስፈፀም አቅም የሌለው ስለሆነ ተቋሙ የራሱን ህልውና ማስከበርም አልቻለም። ይህ የፍትህ ማዕከል ለሙስሊሙ ጥቅም ይሰጥ ዘንድና ሙስሊሙም እምነቱ በሚያዘው መልኩ ፍትህን እንዲያገኝ አስፈላጊው የመርህም ሆነ የአፈጻጸም መሻሻል ተደርጎበት እንደማንኛዉም ፍርድ ቤት በሕገ-መንግስቱ የተሰጠውን ሀላፊነት ተግባራዊ ያደርግ ዘንድ እንጠይቃለን።

### *ሐ. ሙስሊሙ ያለ ልዩ ተፅንዖ የኃይማኖት ቦታ በማግኘትና መስጊድ በመገንባት እምነቱን በነፃ የመተግበር መብቱ ይጠበቅለት፤*

መስጊድ ለሙስሊሙ ሕይዎት ወሳኝ ተቋም ነው። የሙስሊሙ ማህበረሰብ የኃይማኖት ባህሪ በወጉ መጤን ይኖርበታል። መስጊድ ከሙስሊሙ የእለት ከእለት ህይዎት ጋር በእጅጉ የተጣመረ ነው። የዚህን ተቋም ህልውና የማይቀበል መንግስት በሰፊው የሙስሊም ማህበረሰብ ዘንድ ተአመኔታን ሊያገኝ አይችልም።

ሙስሊሞች እምነታቸውን ለመተግበር አስፈላጊ የሆነ የመስጊድ ቦታ ለማግኘትና በህጋዊ መንገድ ቦታ አግኝተው መስጊድ ለመገንባት የተለያዩ ችግሮች እያጋጠማቸው ነው። በተለይም በአዲስ አበባ የሙስሊም ደም ሳይፈስ ሁከት ሳይፈጠር የተሰራ መስጊድ ጥቂት ነው። ይህ የዜግነትን ሰሜት በእጅጉ የሚሸረሽር ነው።

በሀገራችን ታሪክ ከዋናው ኢትዮጵያ አካል የመገንጠል ንቅናቄ */Separatist Movement/* የተነሳውና እየተነሳ ያለዉም በአብዛኛው ሙስሊም ከሆነው አካባቢ ነው። ለምን ብሎ መጠየቅ አስፈላጊ ነው። መገለል፣ የዜግነት መብት አለመከበር ያመጣው ጦስ ነው - በአብዛኛው። ስለዚህ ይህን እጅግ መሰረታዊ የሆነ መንግስትም በቀላሉ ተግባራዊ ሊያደርገውና ከዜጎቹ ጋር በሰላም ሊያኖረው የሚችለውን ጥያቄ - የመስጊድ ቦታና ግንባታን - ምላሽ እንዲሰጥ እንጠይቃለን።

### *መ. በበርካታ የሀገሪቱ የትምህርት ተቋማት ዉስጥ በሙስሊም ተማሪዎች ላይ የሚደረገው ማዕቀብ ይወገድ፤*

ትምህርት የአንድ ሀገር እድገትና ብልፅግና መሰረት ነው። ያልተማረ የህብረተሰብ ክፍል ይዞ በማንኛዉም መልክ ለውጥን ማምጣት አይቻልም። መንግስትም ይህን ችግር በመገንዘብ ይመስለናል ትምህርትን በሰፊው ለማዳረስ የሚያስችሉ እርምጃዎችን እየወሰደ ያለው። ከነዚህም እንደሌሎች ኋላቀር የህብረተሰብ ክፍል ሁሉ ሙስሊሙም ተጠቃሚ ሆኗል።

በአንደኛና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የምናየው የሙስሊሙ በትምህርት ተሳትፎ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ዉስጥ ለማየት አልተቻለም። ለዚህም የተለያዩ ምክንያቶች ሊኖሩ ቢችሉም አንዱ እና እጅግ አሳሳቢ እየሆነ የመጣው በእነዚህ ተቋማት ዉስጥ በሙስሊሙ ተማሪ ላይ የሚደረጉ ጫናዎችና የሙስሊሙ ተማሪን ማንነት ጥያቄ ዉስጥ የሚያስገቡ የአሰራር ደንቦችና የሚወሰዱ እርምጃዎች ናቸው።



*በውጭ ከሚኖሩ የኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ማህበራት*
*ለጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የቀረቡ ጥያቄዎች*

በተለያዩ የትምህርት ተቋማት ሙስሊም ተማሪዎች ሰላት እንዳይሰግዱ ተከልክለዋል። ሴቶች እህቶቻችን እና ልጆቻችን በግቢያቸው ዉስጥ በኃይማኖታቸው ግዴታ የሆነባቸውን ሂጃብ (እስላማዊ አለባበስ) እንዳይለብሱ ታግደዋል። እነዚህና መሰል እርምጃዎች ሙስሊሙን ተማሪ በመንታ መንገድ ላይ እያስቀመጡ ነው - በትምህርቱና በማንነቱ መካከል ምርጫ እንዲያደርግ በመገደዱ።

እነዚህ በህዝብ ገንዘብ የሚተዳደሩ ተቋማት የሙስሊሙን ህብረተስብ እምነትና ባህል ከግምት ማስገባት አለመቻላቸው ተቋማቱ የአንተ አይደለንም የሚሉ ሆነው አገኝተነዋል። እርምጃዎችም ሙስሊሙን ከዚህ መሰረታዊ ተቋም ለማግለል ይወስዱ የነበሩ እርምጃዎች ቀጣይ ሆነው ታይተዋል። ከዚህም በተጨማሪ በማደግ ላይ ባለውና የነገይቱ ኢትዮጵያ ተስፋ በሆነው የወጣቱ ለጋ አዕምሮ ለሀገርም ሆነ ለወገን አደገኛ የሆነ በሽታ ሊተክሉ የማይችሉበት ሁኔታ አይታየንም።

እንደሚታወቀው አንድ ሰው ሙስሊም ለመባል ማሟላት ያለበት ግዴታዎች አሉት። ከእነዚህም መካከል ሰላት አንዱ ነው። ሰላት ከአምስቱ የእስልምና መሰረቶች ዉስጥ ሲሆን በሰአት የተገደበና በቀን አምስት ጊዜ የሚሰገድ (የሚተገበር) በእያንዳንዱ አማኝ ላይ የተጣለ ግዴታ ነው። በሴቶች እህቶች ላይ ግዴታ የሆነው የእስላማዊ አለባበስ (ሂጃብ)ም በኃይማኖቱ ትልቅ ቦታ የተሰጠው ነው።

በትምህርት ተቋማት ውስጥ ማንኛዉንም ዓይነት ኃይማኖታዊ እንቅስቃሴ ማድረግ አይቻልም የሚል እርምጃ እኩልነትን አንፀባራቂ ቢመስልም ከሙስሊሙ ተማሪ አንፃር በምንም መልኩ ፍትሃዊ ሊሆን አይችልም። የሌሎች እምነት ተከታዮች የኃይማኖት ግዴታዎቻቸውን ከትምህርት ሰዓት ውጭ መወጣት ሲችሉ ሙስሊሙ ተማሪ ግን ሰላቱ በሰዓት የተገደበ በመሆኑ ከትምህርቱ ወይም ከሰላቱ እንዲመርጥ ይገደዳል። ሙስሊሙ ሰላቱን በግቢው ውስጥ መስገድ ካልቻለ ትምህርቱን መከታተልና የኃይማኖት ግዴታውንም መወጣት አይችልም። እንደዚሁም ሴቷ ሙስሊም ልብሷን ሳትለብስ ትምህርት መከታተል አትችልም። ትምህርት ቤቶችና ተቋማት ህብረተሰቡን ለማገልገልና ሀገር ገንቢ የሆነ ትዉልድ ለማፍራት የቆሙ ከሆነ የሚያገለግሉትን ህብረተሰብ ባህልና እምነት ከግምት ማስገባት አለባቸው ብለን እናምናለን። ይህን ማድረግ የማይችሉ ከሆነ እነዚህ የህዝብ ተቋማት የተወሰነውን የህብረተሰብ ክፍል በተለይም ሙስሊሙን ተማሪ ለማስተናገድ ዝግጁ አለመሆናቸውን ብቻ አረጋጋጭ ናቸው።

## 3. ሀገራችን በእስልምና ኃይማኖት ካላት ልዩ ቦታ ተጠቃሚ ትሆንና በዚህም ምክኒያት ለአለም ሰላም የሚኖራት አስተዋፅዖ ይጎለብት ዘንድ መንግስት አስፋላጊውን ጥረት ያድርግ፤

ሀገራችን ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊያን ለእስልምና እምነት እድገትና አድጎም ለመጎልበት ልዩ አስተዋፅዖን አድርገዋል። ከዚህም የተነሳ ሀገራችንና ዜጎቿ በእስልምና ታሪክ ዉስጥ ልዮ ቦታን ሊይዙ፣ አኩሪ ክብርና ዝናንም ሊጎናፀፉ ችለዋል። በእስልምና ታሪክ ዉስጥ ሀገራችን ያላት ገድልም ለኛ ኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን ለአለም ህዝቦች ከእምነት ጋር በተያያዘ የሚከሰቱ ችግሮችን ለመፍታት ወደር የሌለው ምሳሌ አስቀማጭ ነው።

የእስልምና ሐይማኖት ወደ ሀገራችን የገባው በመካ ከተማ እንኳን ይፋ ጥሪ ከመደረጉ በፊትና የእስልምና የዘመን አቆጣጠር ከሚጀምርበት ሂጂሪያ ሰባት አመታት ቀደም ብሎ ነው። በዚህም ሀገራችን ከማንኛውም ሀገር በፊት እምነቱ የገባባት ሀገር ለመሆን በቅታለች።

ነብዩ (የአላህ ሰላምና እዝነት በእርሳቸው ላይ ይዉረድ) “ወደ ሐበሻ ሂዱ” ብለው በእምነታቸው ምክንያት ስቃይና መከራ የበዛባቸው ተከታዮቻቸውን ባዘዙበት ወቅት ይህችን የሙስሊሞች የመጀመሪያ የስደት ሀገርና አስተዳዳሪዎቿን የገለጹት፦

> *“በሐበሻ ሀገር አድሎ የማያደርግ ሀቀኛ ንጉስ አለ። የእዉነት ሀገርም በመሆኗ ወደዚያች ሀገር ሄዳችሁ ብትጠለሉ እዚህ ካጋጠማችሁ ጭንቀትና ችግር ልትድኑ ትችላላችሁ”*

በማለት ነበር።

ሀገራችን ስደተኞችን ፍትህ ወደማያገኙበት ሀገርና የአስተዳደር ስርዓት አሳልፎ ባለመስጠት የመጀመሪያዋ ነች ለማለት በቂ መረጃ ባይኖረንም ከዚህ ጋር በተያያዘ ለአለማችን ልዩ አስተምህሮቶችን እንደቸረች ይታመናል። ለተለያዩ የተባበሩት መንግስታት መመሪያዎችና የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎች መነሻም ይህ ክስተትና አኩሪ ታሪካችን እንደሆነ አመልካች መረጃዎች አሉ። ከነዚህ መመሪያዎችና ድንጋጌዎች መካከል የሰብአዊ መብት መከበር የሚዳስሡ አንቀጾች፣ ሙስናን መዋጋት፣ የተበደሉና በሀገራቸው ፍትህና ነጻነት ላጡ ዜጎች መጠለያ መስጠትና እንክብካቤ ማድረግ፣ የሰው ልጅን እኩልነት ማረጋገጥ፣ የእምነት ነጻነትና የመሳሰሉት ተጠቃሾች ናቸው።

በስደት የመጡ ሙስሊሞች ከሌሎች ኢትዮጵያዊያን ጋር በሰላም በመኖር እምነታቸውንም ከኢትዮጵያዊያን ጋር በመቋደስ በርካታ አማኞችን በማፍራት እምነቱ እንዲያድግና እንዲስፋፋ መሰረት መጣል መቻላቸው ብቻ ሳይሆን የወቅቱ ንጉስ “ንጉስ አስሃማ” እስልምናን መቀበሉ ሀገራችን የእውነትና የፍትህ ሀገር ከሚሉት መገለጫዎች በተጨማሪ የእስልምና እምነት በአስተዳደር ደረጃ እውቅና አገኝቶ ንጉሷም እምነቱን የተቀበለበት የመጀምሪያዋ ሀገር በመሆን ላቅ ያለ ቦታ ተችሯታል።

በዚሁ ስደት ወቅት ሀገራችን ከታዋቂ የነብዩ ባልደረባዎች መካከል የነብዩ ባልተቤቶችንም ለማስተናገድ በመታደሏ “የሙስሊም እናቶች ሀገር” የሚል ማዕረግ ትጎናፀፋለች።

ከእስልምና እምነት መግባት ጋር በተያያዘ ካፈራችው አኩሪ ታሪክ በተጨማሪ ሀገራችን ሌሎች አኩሪ ገድሎችም አሏት። የነብያችን አሳዳጊና በራሳቸው ቃል “ከእናቴ በኋላ እናቴ (ዑሚ በዕደ ዑሚ)” በማለት የገለጿት በረከቱ ሐበሽያ ኡሙ አይመን ወይም በረካ፤ በአለም ላይ ባሉ ሙስሊሞች ዘንድ በትንሹ በቀን አምስት ጊዜ ስራው እስከ አለም ፍጻሜ ድረስ የሚተገበረውና የሚታወሰው ቢላል አል-ሀበሻ፤ እንደዚሁም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ለእምነቱ ስር መስደድ፣ ማደግና መስፋፋት ልዩ አስተዋፅዖ ያደረጉ በርካታ የኢትዮጵያ ልጆች ሀገራችን ከእስልምና ታሪክ ዉስጥ ያላትን ቦታ ከፍ አድርገዉ እና ከእምነቱም ጋር ያላትን ትስስር አጠንክረዉት ይገኛል።

ይህ አይነት አኩሪና የተቀደሰ ታሪክ ለብዙዎች ያልታደለ በመሆኑ ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች በልዩ ክብር ሲይዙት ሀገራችንም ይህንኑ ወደር የሌለው ልገሳ ልትንከባከበው፣ ልታሳድገውና ለአለምም ልታሳውቀው ይገባል። በእስልምና ታሪክ ዉስጥ ያለን ገድል አስፈላጊውን ትኩረትና ተገቢው እንክብካቤ ተደርጎለት ከቀረበ ለአለም አጠቃላይ ሰላም በተለይም ለሰው ልጆች እኩልነት፣ መቻቻልና መከባበርን በተመለከተ የሚያደርገው አስተዋፅዖ ቀላል አይደለም።

አስፈላጊውን ትኩረት ተሰጥቶ መንቀሳቀስ ከተቻለ ሀገራችን በእስልምና ውስጥ ካላት ቦታ ተጠቃሚ ልትሆን የምትችልባቸው በርካታ መንገዶች አሉ። አስቸኳይ እርምጃን ይሻሉ ከምንላቸውና መንግስት ትኩረት እንዲሰጣቸው ከምንጠይቃቸው መካከል፦





### *ሀ. ሀገራችን የሙስሊም ሀገሮች ማህበር /Organization of Islamic Countries, OIC/ አባል ትሆን ዘንድ መንግስት ጥረት ያድርግ፣ አስፈላጊውንም እርምጃ ይውሰድ፤*

ሀገሪቱ ካላት የህዝበ ሙስሊም ብዛት አንፃርም ይህን ከእምነቱ ጋር ካላት የጠበቀና መሰረታዊ የሆነ ትሥሥር ኢትዮጵያ የዚህ ማህበር አካል መሆን የማትችልበት ምክንያት የለም። ከዚህም እስካሁን በአግባቡ ልታገኝ ያልቻለችዉን በኢኮኖሚዉም ይሁን በፓለቲካው እንደዚሁም በእስልምና ያላትን የላቀና አኩሪ ቦታ ዳግም ትይዝ ዘንድ ይረዳል ብለን እናምናለን።

### *ለ. የሀገሪቱን እስላማዊ ታሪክ የሚያጠኑ፣ አዘጋጅተው የሚያቀርቡና የሚጠብቁ ተቋሞችና ማዕከላት ይቋቋሙ፤*

ሀገራችን ያላት እስላማዊ ታሪክና ገድል ለኛ ኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን ለአለም ህዝቦች ከእምነት ጋር በተያያዘ አለማችን ያሉባትን ችግሮች ለመፍታት ወደር የሌለው ምሳሌ አስቀማጭ እንደሆነና በተለይም በሰላም ተከባብሮ መኖርና መቻቻልን በተመለከተ ይህ ነው የማይባል አስተዋጽዖ እንደሚኖሯት ቀደም ብለን ጠቁመናል።

የሰው ልጆች ለተለያየ ጉዳይ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ምክንያት የተለያዩ እምነት፣ ዘር፣ ባህልና ታሪክ ያላቸው ህዝቦች ግንኙነት ጨምሯል። ይህም ከራሱ ጋር በእምነቶችና ባህሎች መካከል ውጥረትን ፈጥሮ ለመፍትሄ ፍለጋ ምሁራን እንደዚሁም መሪዎች ያላሰለሰ ጥረት እያደረጉ ይገኛል። በበርካታ ሀገሮች ችግሩ ከፍተኛ ትኩረትን በማግኘት የሀገሮችን የፓለቲካና የማህበራዊ ኖሮ በአዲስ መልክ እየቀየሰ ይገኛል። ለዚህ ችግር ዘላቂ መፍትሄ ለማግኘት በሚደረገው ጥረት ሀገራችን ያላት እስላማዊ ታሪክ የሚኖረው አስተዋጽዖ ቀላል አይሆንም። ይህንም እዉነታ በመረዳት ይመስላል የተለያዩ ምሁራን “የአቢሲኒያ ምሳሌ” */the Abyssinian Model/* የሚል ንድፈ-ሃሳብ በማቅረብ ሀገሮችና መንግስታት የሀገራችንን እስላማዊ ታሪክ እንደምሳሌ እንዲወስዱ ጥረት እያደረጉ ይገኛል።

ከዚህም የምንረዳዉ እስላማዊ የሀገራችን ታሪክና ቅርስ በወጉ ተጠንቶ እንዲቀርብና እንዲጠበቅ የሚያስችሉ የምርምር ተቋማት፣ ማዕከላት፣ ሙዚየሞች፣ ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች አስፈላጊ መሆናቸውን ነው። እነዚህ ተቋማት ሀገሪቱ ለዘመናት ባለፈችበት “የአንድ እምነት” ፖሊሲ ሰለባ ለሆኑ ዜጎችና ድርጅቶች እስላም እንደ ኃይማኖት ለሀገራችን ገንቢ ሚና ያለው አዎንታዊ ኃይል */Positive Force/* መሆኑን እንዲገነዘቡት በማስቻል በኩል የሚኖራቸው ጥቅም ቀላል አልነበረም። እዚህ ላይ ልናፍርበት የምንገደደው አለም ለወቅታዊ ችግሮቹ መፍትሄን በመሻት ፊቱን ወደ እኛ እያዞረ ባለበት ወቅት ሀገራችን ይህን ታሪኳን ክፍት አድርጋ የምታቀርብበት ተቋምና ማዕከል ሊኖራት ይቅር እና አንጋፋ በሆነው የሀገሪቱ ዩኒቨርሲቲ እንኳ የእስላማዊ ጥናት የትምህርት ክፍል የለም።

አሁንም ሀገራችን ይህን በሩቁ ተቀብሮ ያለ ታሪኳን ማዉጣት አለባት። ለዚህም የሚያገለግሉ ተቋማትን አስፈላጊውን ትኩረት ሰጥታና በጀት መድባ መገንባት ይኖርባታል። አለማቋቋሙ የተያያዝነውን የብዙሃናዊነት ሥርዓት የሚፈታተን ነው። ይህ ጉዳይ የዜጎችን የማንነት ጥያቄ ምላሽ ከመስጠትና ታሪክን አሳድጎና ጠብቆ ለቀጣይ ትውልድ ከማስተላለፍ ጋር የሚገናኝ በመሆኑም መንግስታችን ትኩረት እንዲሰጠው እንጠይቃለን። በዚህ ረገድ ለመንቀሳቀስ የሚፈልጉ የግል ባለሃብቶችንም /በግልም

ይሁን በማህበራት/ በማበረታታት መንግስት አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያደርግላቸው በተጨማሪ መጠየቅ እንወዳለን።

## 4. መንግስታዊ ያልሆኑ እስላማዊ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ያለልዩ ተፅንዖ እንድንቀሳቀሱ ይሁን፤

የሀገራችን ኢኮኖሚያዊ አቅም ዉስን እንደመሆኑ መጠን ከፍተኛ ኃይማኖታዊና ማህበራዊ ፕሮጀክቶች በሀገር ውስጥ ብቻ ማንቀሳቀስ እንደማይቻል እሙን ነው። በመሆኑም መንግስታዊና ሀገር በቀል ያልሆኑ የኃይማኖትም ሆኑ የልማት ድርጅቶች */NGO/* ሙስሊሙም ያስፈልጉታል። እነኝህ ድርጅቶች ከምዕራቡም ከምስራቁም ዓለም መንግስታዊ እውቅና ሳይኖራቸው በሀገራችን ለመንቀሳቀስ የማይመጡ መሆኑን እንገነዘባለን። በመሆኑም በአስጊነት መፈረጅ አለባቸው ብለን አናምንም።

በሀገራችን በአሁኑ ሰዓት በልማት ስም የተመዘገቡ በርካታ የረድኤት ድርጅቶች በክርስቲያናዊ ተራድኦ ድርጅት */CRDA/* ስም ተመዝግበው ሲንቀሳቀሱ የሙስሊሙ የረድኤት ድርጅቶች ግን በተፅንዖ ስር ወድቀዋል። በየጊዜው ወደ ሀገር ዉስጥ የገቡት ጥቂት የውጭ እስላማዊ የረድኤት ድርጅቶችም ከስመዋል። አሁን አሉ የሚባሉት ጥቂት የረድኤት ድርጅቶችም ሕልውናቸው ተመናምኗል። ለምን?

በኃይማኖት ስም ፈቃድ ያገኙ የውጭ ሙስሊም ድርጅቶች ስለመኖራቸው መረጃ የለንም። ከክርስቲያኑ ወገን ግን በመቶዎች የሚቆጠሩ ስለመኖራቸው በቂ መረጃ አለ። ይህ ተቋማዊ የሚዛናዊነት ጉድለትን ያመላክተናል። ተቋማዊ ሚዛን አልባነት */Institutional Imbalance/* ባለበት ሀገር ደግሞ ጭቆና የለም ለማለት አያስደፍርም። ለለውጥ የቆመው ይህ መንግስት እንዲህ ዓይነቱን አሰራር ማስቀረት ይጠበቅበታል። ህዝበ ሙስሊሙ ተቋም አልባ በሆነ ቁጥር ለድህነት ይጋለጣል። ለስነ ልቦናዊ አለመረጋጋት ይዳረጋል። መቆጣጠር አስቸጋሪ የሆነ ስንኩል አመለካከት ውስጥ የሚዘፈቁ ኃይላትን በውስጡ ይፈጥራል። ሌላም ሀገሪቱ ልትሸከመው ከማትችለው ማጥ ዉስጥ ይገባል።

## 5. የሀገሪቱን ሴኩላር አስተዳደር የሚጻረሩ አሰራሮች ይወገዱ፤

እንደ ኢትዮጵያ ላሉ የበርካታ ብሔር ብሔረሰቦችና ኃይማኖቶች መናኸሪያ ለሆኑ ሀገራት ሴኩላሪዝም የተሻለ አማራጭ ለመሆኑ አከራካሪ አይደለም። ከዚህ መሰረታዊ እዉነታ በመነሳት ሀገራችንም ይህኑ በሕገ-መንግስቱ ውስጥ አስቀምጣለች።

በሕገ-መንግስቱ የተቀመጠው የሀገሪቱ ሴኩላርነት ትርጉም የሚሰጠው መንግስትና የመንግስት አዉታሮች ከኃይማኖታዊ አድሎአዊነት ነፃ የሆነ ግልጋሎት ለህብረተሰቡ መስጠት ሲችሉ ነው። ከዚህም በተጨማሪ እነዚህ ተቋማት ለአንድ እምነት መስፋፊያ መሳሪያ እስካልተደረጉ ድረስም ነው። በስልጣን ላይ ያሉ አካላትም የተቀመጡበትን ወንበር አንዱን ደግፈው ሌላዉን ለማዳከም እስካልተጠቀሙበት ነው። ዜጎች በፍርድ ሂደትና አፈጻጸም ላይ በኃይማኖታቸው ምክንያት አድሎ ሳይደረግባቸው ሲቀር ነው። በሀገር ጉዳይና ልማት ላይ ለመሳተፍ እንደዚሁም የዜጎች ለሀገራቸው ያላቸው ፍቅርና ውዴታ ኃይማኖት እንደመለኪያ ማገልገሉ ሲቆም ነው። እንግዲህ እነዚህና መሰል የሴኩላሪዝም መገለጫዎች ካልታዩ የአንድ መንግስት በወረቀት ላይ ሴኩላር ነኝ ማለት በራሱ ሴኩላር ሊያደርገው አይችልም። በተለይም ሙስሊሙ በወረቀት ላይ በተቀመጡ ነገር ግን ተግባራዊ መገለጫ በሌላቸው መብቶች በእጅጉ ተሰላችቷል።





በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች እና በተለያዩ ጊዜያት የተወሰዱ እርምጃዎች ይህ በሕገ-መንግስቱ የተቀመጠው የኢትዮጵያ መንግስት ሴኩላርነት ከወረቀት ማለፉን ጥያቄ ውስጥ አስገብተዉታል። በመርህ ደረጃ መንግስትና ኃይማኖት ከአፄ ኃይለ ስላሴ መውደቅ ጋር የተገረሰሰ ቢሆንም ፍልስፍናው ግን በተግባር ገና የለቀቀን አይመስልም። ይህንም ግልፅ ለማድረግ የሚከተሉትን ሁለት ማስረጃዎችን ለመጥቀስ እንወዳለን፡-

*i.* የአክሱም ከተማና አካባቢው
*ii.* የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት።

### *i - አክሱም ከተማና አካባቢው፡-*

አክሱም ለክርስትያኖች ታሪካዊ ቦታ እንደሆነች ሁሉ ለሙስሊሞችም ታሪካዊ ነች። እስልምና ሀገራችን በገባበት ወቅት በመጀመሪያ የገባው አክሱም ነው። የሀገራችን የፍትህ፣ የመቻቻልና የመከባበር ምሳሌነት ተገላጭ የሆነዉም በአክሱም ነበር። የኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ታሪክ መጀመሪያዉም ከሌላ ሳይሆን ከአክሱም ነው።

የአክሱም ሙስሊሞች በአገሪቱ ለዘመናት የኖረውን የሙስሊሞች ስቃይና ስቆቃ መገለጫ ናቸው። ምንም እንኳን በ10 ሺዎች የሚቆጠር ሙስሊም በከተማዋ ቢኖርም ሙስሊሞች የሚፀልዩበት አንድ እንኳን መስጊድ የለም፤ ልጆቻቸውን የሚልኩበት የኃይማኖት ትምህርት ቤት የላቸዉም። የአካባቢው ተወላጆች በአካባቢያቸው ልማትና እድገት ለመሳተፍ ቢጥሩም እድሉን ተነፍገዋል። በተለያዩ ጊዜያት ለችግሮች እልባት ለማግኘት ቢጥሩም በስልጣን ላይ ያሉ አካላት ሕገ-መንግስቱን ገቢራዊ ለማድረግ ፈቃደኛ አልሆኑም። ሙስሊሞች ለሚያቀርቡት የፍትህና የመብታችን ይከበርልን ጥያቄም የተሰጡ መልሶች እነሱና እምነታቸው ተቀባይነት እንደሌላቸው ገላጮች ናቸው። “አካባቢውን ከጴንጤና ከሙስሊም ማፅዳት” የሚል ዘመቻ እየተካሄደ እንደሆነም በባለስልጣኖች በተደጋጋሚ ተገልጾ ሙስሊሞች ስለ እምነት እኩልነትም ሆነ ሕገ-መንግስታዊ መብት መከበር የሚያደርጉት ጥረት ዋጋ ቢስ በመሆኑ በከንቱ እንዳይለፉ ተመክረዋል። ለአካባቢያቸው ልማት በማሰብ፣ ሕገ-መንግስታዊ መብታቸውን ተጠቅመውና ህጋዊ መንገድን ተከትለው ለልማት ቢንቀሳቀሱም “እናንተ የሙስሊም ማህበር በመሆናችሁ (ልማት) በእናንተ መሰራት የለበትም” በመባል ለትምህርት ቤት ግንባታ ከከተማው ማዘጋጃ ቤት በተረከቡት ቦታ ላይ የጀመሩትን ፕሮጀክት እንዲያቆሙ ተደርጓል። ይህ በህጋዊ መንገድ ያገኙት ቦታም ከነቁሳቁሱ ተወርሷል። በአክሱም ከተማ ሙስሊሞች የመጸለያ ቦታ ለመስራት መቻል ይቅርና ጥያቄውን እንኳን በሚያቀርብ ግለሰብ ላይ እርምጃ እንደሚወሰድ በተለያዩ የክልሉ ከፍተኛ ባለስልጣኖች በኩል ተገልጿል። በተደጋጋሚ “የአጼ ኃይለ ስላሴን ስርዓትና አካሄድ ይዞ ከመጓዝ ዉጭ ሌላ አማራጭ አለመኖሩን”፤ ሙስሊሞችም “በደርግና በአጼ ኃይለ ስላሴ ያልተደረገ ነገር መጠበቅ” እንደሌለባቸው በማያሻማ መልኩ ግልፅ ተደርጓል። ይህ በተከታታይ የተከሰቱ ጨቋኝ ስርዓቶችን ለማስወገድ በተዋደቁ የኢትዮጵያ ልጆች ደም ላይ ውሃ የቸለሰ ነው። ችግሩ ለበላይ ባለስልጣናት እስከ ጠቅላይ ሚኒስትር ፅህፈት ቤት ድረስ አቤት ቢባልምና በተለይም በጠቅላይ ሚኒስትሩ በኩል ቀና አመለካከት የተገኘ የነበር ቢሆንም እልባት ግን ሳያገኝ ቀርቷል። እንግዲህ እነዚህ እና ሌሎች መሰል አቋሞችና ድርጊቶች ባሉበት ሁኔታ በተለይ በአክሱም ከተማና አካባቢው የሀገሪቱ ሕገ-መንግስት የሚደነግገው ሴኩላራዊነት ከወረቀት ያላለፈ መሆኑን ያስረዳሉ።

### ii - ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት፡-

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በክልሉ ፕሬዝዳንት ፅህፈት ቤት የሚመራ አንድን እምነት ብቻ እውቅና የሚሰጥና የሚያጎለብት ሌላዉን ደግሞ ለማጥፋት ያቀደ እንቅስቃሴ እየተካሄደ ነው። ፅህፈት ቤቱ በአለም ላይ ለሚንቀሳቀሱ ሚሲዮናዊያን ላቀረበው የድረሱልኝ ጥሪ ብሌየር ፋዉንደሺን */Blair Foundation/* ከተሰኘ የአሜሪካ የሚሽነሪ ድርጅት ምላሽ አገኝቷል። በዚህም አንድ ሺህ ቤተክርስቲያን በሁለት አመት ዉስጥ ለመገንባት የሚያስችል ገንዘብና እና የክልሉን ህዝብ በዚሁ ጊዜ ዉስጥ ክርስቲያን ለማድረግ በሚል አላማ ሌሎችም እርዳታዎችን ለማግኘት ችሏል። ፕሬዝዳንቱ የስልጣን ጊዜያቸዉን ክልሉን ከማልማት ይልቅ እምነታቸውን በድሃው ህብረተስብ ላይ ከተቻለ በማታለል ካልተቻለም በግዳጅ ለመጫን ቆርጠው እንደተነሱ፤ በቦታውም የተቀመጡት ለዚሁ አላማ መሆኑንና ይህንም ከስልጣን ከመውረዳቸውና በሌላ ከመተካታቸው በፊት ከግብ ማድረስ እንዳቀዱ በተለያየ ጊዜ ከሰጡት መግለጫ ታዉቋም። ይህም ፕሬዝዳንቱንና ፅህፈት ቤቱ የቆሙለት አላማ ሚስጢራዊ እንዳልሆነና የክልል መንግስቱ ፖሊሲ መሆኑን ያስረዳናል።

ከላይ ያቀረብናቸው በአክሱም እና በቤኒሻንጉል ጉምዝ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የሚካሄዱት ከኃይማኖት ነጻ ያልሆኑ አሰራሮች በሥልጣን መባለግ ብቻ የሚታዩ ናቸው ብለን አናምንም። ይልቁንስ ሀገሪቱ በሕገ-መንግስቱ ዉስጥ ያስቀመጠችው ሴኩላር አስተዳደር በሁሉም የአገሪቱ ክፍል ተቀባይነትና ተፈፃሚነት ያጣ መሆኑን ያስገነዝቡናል። አሁንም መንግስት ኢትዮጵያን ሊታደግ የሚችለው ራሱን ሙሉ በሙሉ ከኃይማኖት በመገንጠል ሕጉንና ፖሊሲዉን ሁሉ-አቀፍ በሆኑ ድሞክራሲያዊ መርሆዎች ላይ ሲገነባና ይህንኑም ተግባራዊ ሲያደርግ ነው። እነዚህ አሰራሮች ከድሞክራሲያዊ ስርዓትና ሕገ-መንግስቱ ጋር የማይጣጣሙ በመሆናቸው አስቸኳይ ማስተካከያ እንዲደረግባቸው፣ የሕገ-መንግስታዊ ስርዓትን ለመከተልና ለማስፈጸም ፈቃደኛ ያልሆኑ የመንግስት አካላት ለፍርድ እንዲቀርቡ እንጠይቃለን። በዚሁ አጋጣሚ ይህ ጉዳይ እልባት ማግኘት አለመቻሉ ሀገራችን በልማትና ብልፅግና የምታደርገውን ጥረት እንደሚገታና በህዝባችን ዉስጥ አላስፈላጊ አደጋን ሊያስከትል ይችላል የሚል ፍራቻ ያለን መሆኑን ጨምረን መግለፅ እንወዳለን።

## 6. የተዛባው የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ቁጥር ይስተካከል፤

ገዥዎች ኢትዮጵያ "የኢትዮጵያዊያን ደሴት" ገፅታን እንዳትላበስ ለማድረግ ከወሰዱት በተለይም የሙስሊሙን ህልውና ለመካድ ከተጠቀሙባቸው መንገዶች አንዱ ቁጥራቸውን አሳንሶ ማቅረብ የሚለው አንዱ ነበር። አሁን ባለው መንግስት እውቅና ያለው የሙስሊሞች ቁጥርም ይህን ብሶት ሊቀይረው አልቻለም። በተቃራኒው በመጨረሻዉ የህዝብና ቤቶች ቆጠራ መሰረት የሙስሊሙ ቁጥር ከጠቅላላው የሀገሪቱ ህዝብ ብዛት አንድ ሶስተኛ እንኳን እንዳልሆነ እንገነዘባለን። ይህ አሀዝ ከዚህ በፊት እውቅና ከነበረውና የሙስሊሙን ቁጥር ወደ 45% ከሚገምተው አሀዝ በእጅጉ አንሶ እናገኘዋለን። የዚህን ክስተት ትንታኔ ጉዳይ ለባለሙያዎች ተወት አድርገን ቁጥሬ እንዲያንስ ተደርጓል በዚህም የተነሳ የኢትዮጵያዊያን ልጆች አጥንታቸውን ከስክሰው ደማቸውን አፍሰው እውን ባደረጉት የድሞክረሲ ስርዓት ዉስጥ አግባብ ያለው ውክልና እንዳይኖረኝ፣ በሀገሬ ጉዳይም ላይ ተገቢውን ቦታ እንዳልይዝ ተደርጌያለሁ የሚለው የሙስሊሙ የብሶት ጥያቄ ግን ከጊዜ ወደ ጊዜ ስር እየሰደደ ይገኛል።





በመንግስት እውቅና ያለው የሙስሊሞች አሃዝ በአለም አቀፍ ደርጃ ውድቅ ተደርጓል። መንግስታዊ ያልሆኑ አለም አቀፍ ድርጅቶች የሰበሰቡትን መረጃ ድጋፍ በማድረግ ባሰሉት ስሌት መሰረት ሙስሊሙ ከ45-50% እንደሚሆን በመገመት በሀገሪቱ ውስጥ የበላጭነትን ደረጃ ይሰጡታል። ይህም ሁኔታ መንግስት ይፋ ባደረገው አሃዝ ላይ ሙስሊሙ ያለውን ጥርጣሬ አጠናክሮት ይገኛል።

አንዲት ሀገር በተለያዩ የኑሮ ዘርፎች እድገትንና መሻሻልን ታመጣ ዘንድ በመንግስትና በዜጎች መካከል መተማመን መኖር ወሳኝ ነው። የህዝቦችን ቁጥር በተመለከተ ህዝቦች በመንግስት ላይ ያላቸው አለመተማመን እንዲቀጥል መደረግ የለበትም። ይህ ሊወገድ የሚችልበት ወሳኝ ወቅትም ላይ እንገኛለን። በአጭር ጊዜ ውስጥ ሀገር አቀፍ የህዝብና ቤቶች ቆጠራ ይካሄዳል። ይህም ቆጠራ ነባር ለሆነው የዜጎች ጥያቄ ተአመኔታነት ባለው መልኩ እልባት ይሰጥ ዘንድ ልዩ ትኩረት ሊቸረው ይገባል። ዜጎች ሰለ ቆጠራው አስፈላጊነትና ጥቅም ትምህርት ያስፈልጋቸዋል። በተለይ ሙስሊሙ ልዩ ትኩረትን ይሻል። ከዚህም በተጨማሪ በፌደራል ደረጃ ከዚያም በተዋረድ በተለይ ከሁለቱ እምነቶች የተውጣጣና በህብረተሰቡም ዘንድ ተወካይነት የሚኖራቸው ግለሰቦችን ያቀፈ ገለልተኛ አረጋጋጭ/ታዛቢ አካል ማቋቋም አስፈላጊነቱ የጎላ በመሆኑ ለዚህ ገቢራዊነት መንግስት አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወስድ እንጠይቃለን።

## 7. የዜጎችን እምነትና ባህል ያገናዘበ የመገናኛ ብዙሃን አጠቃቀም ገቢራዊ ይሁን፤

ለአንድ ሀገር ሰላም እና መረጋጋት ብሎም እድገትና ብልፅግና የመገናኛ ብዙሃን ወሳኝ ሚናን ይጫወታሉ። ይህ መልካም ሚናቸው እውን የሚሆነው የሚያቀርቧቸው ዘገባዎች እውነታን የተሞረከዙና ሚዛናዊነትን የተላበሱ ከሆኑ፣ የህዝብን ሰላም እና አብሮ መኖርን እስካላፋለሱ ድረስ ነው። ለዚህም ሲባል የመገናኛ ብዙሃን አጠቃቀም የሀገርን ተጨባጭ ሁኔታ፣ የህዝቦችን ታሪክ፣ ባህል እና እምነት ማገናዘብ ይኖርበታል። አንዱን የህብረተሰብ ክፍል ከሌላው የሚያጋጩ፤ አንዱን ወገን እንደ አጥፊና ሰላም አደፍራሽ አድርጎ የሚያቀርቡ፣ በግልም ይሁን በቡድን የሚፈፀሙ ወንጀሎችን ከኃይማኖት ጋር በማያያዝና ቅዱስ ኃይማኖታዊ ቃላትን በመጠቀም የሚቀርቡ የዜና እወጃዎችና መግለጫዎች ዘላቂ ሰላምን አያጎናፅፉም።

ለዓመታት ያልታረመ የሀገራችን የመገናኛ ብዙሃን ቋንቋ የእስልምናን ኃይማኖት እንደ ኃይማኖትና አማኙን እንደ ህዝብ የስጋት ምንጭ ሆኖ እንዲታይና እንዲታሰብ አስተዋፅዖ አድርጓል። የሙስሊሙንም ሰሜትና ሥነ ልቦና በእጅጉ ጎድቷል። ባለህብቱ እንደልቡ እንዳይንቀሳቀስ፣ ቅኑ የኃይማኖት መምህር ድምፁን እንዳያሰማ፣ መብቱ የተነፈገው ሙስሊም መብቱን እንዳይጠይቅ አንገቱን ያስደፋ ድባብ ፈጥሯል። የኃይማኖት እኩልነት በሕገ-መንግስቱ በተቀመጠበት ዘመንም የኃይማኖት የሥነ ልቦና ጦርነት በሚዲያ እየተፈጸመ ነው። ይህ ለዚህች ድሃ ሀገር የሚፈይዳት ካለመሆኑም በተጨማሪ በዚህ አይነት ሁናቴ ስለ ኃይማኖት እኩልነት መስፈን መግለፅ አስቸጋሪ ይሆናል።

የመንግስት የመገናኛ ብዙሃን ተቋማት ለሙስሊሙ ባህልና ስሜት ትኩረት አልሰጡም ብንል ማጋነን አይሆንም። በሙስሊም በዓላት ተቋማቱ ያላቸውን ሽፋን ብቻ መመልከት በቂ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ እስላማዊ ባህል የሌለ የሚያስመስሉ ዝግጅቶችን የሚያስተናግዱ ናቸው። ሰለዚህ እነዚህ የህዝብ የመገናኛ ብዙሃን የህዝቦችን የባህልና የኃይማኖት እኩልነት እንደዚሁም ክብርን የጠበቁ እንዲሆኑ፤ የህዝባችንንም ሰላም ሊያደፈርሱ ከሚችሉ አሰራሮችና ድርጊቶች እንዲቆጠቡ እንጠይቃለን።

## 8. የኃይማኖት ነክ ጉዳዮች በሚኒስትር ደረጃ ይቋቋም ዘንድ ሃሳብ እናቀርባለን፤

በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች እምነትን ያስታከኩ ግጭቶች ተከሰተዋል። ይህ ሁኔታ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በብዛቱም ሆነ በመጠኑ እየጨመረ መጥቷል። በተለይም በሙስሊሙና ኃይማኖቱ ላይ ያነጣጠሩ ወንጀሎች ተጠናክረዋል። የሙስሊሙን ማንነትና እምነት ተፈታታኝ የሆኑ ወንጀሎች በተከታታይና በተደጋጋሚ ተፈፅመዋል። የእምነቱ መልዕክተኛ በኾኑት ሙሐመድ (የአላህ ሰላም እና እዝነት በእርሳቸው ላይ ይውረድ) ላይ የሥም ማጥፋት ዘመቻዎች በከሚሴ - ወሎ ተካሂደዋል። የሙስሊሞች መመሪያ የሆነው ቁርዓን በተለያዩ የሀገሪቱ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ዉስጥ ተቀዳዷል፤ ለመጸዳጃነት አገልግሎት እንዲውልም ተደርጓል። መስጊዶች ላይ በተለያዩ ጊዜያቶች ጥቃቶች ተሰንዝረዋል፣ ፈርሰዋል፤ ተቃጥለዋል። የሙስሊሙ ታሪካዊና መሰረታዊ የሆኑ ቦታዎች ከሙስሊሙ ላይ ተነጥቀው ለሌላ ተሰጥተዋል። በተለያዩ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ዉስጥ ትምህርታቸውን የሚከታተሉ ሙስሊም ተማሪዎች በደል ደርሶባቸዋል፣ ለእንግልት ተዳርገዋል። እነዚህንም ተከትሎ ዜጎች ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለዋል፣ ንብረት ወድሟል፣ የሰው ነፍስ ጠፍቷል። ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ሕገ-መንግስቱ ለዜጎች የሰጠውን መብት መሰረት አድርገው እምነታቸውን ለመተግበር የሚያደርጉትን ጥረት በውጭው አለም በሚታየው ነገር ግን ከሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ ጋር ምንም ግንኙነት በሌለው ክስተት ለመፈረጅ የሚሞክሩ ኃይሎችም ተበራክተዋል።

ኢትዮጵያዉያን ሙስሊሞች በታሪካቸው አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ መለያ */Identity/* አልነበራቸውም። በአንድ ዘመን ሲደርስባቸው የነበረውን ግፍና ጭቆና በትዕግስትና በሆደ-ሰፊነት አልፈውታል። በሌላ ዘመን ደግሞ ራሳቸውን በገጠሪቱ ክፍል ብቻ ወስነው ከሌላው ወገን ጋር ሳይቀላቀሉ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ተሳትፎአቸውን ገድበው ባህላዊና እምነታዊ ማንነታቸውን ለመጠበቅ ሞክረዋል። በሌላ ዘመንም ክርስቲያናዊ ባህልን ተላብሰው ኖረዋል። አልያም ከላይ የተገለጹትንና ሌሎች መለያዎችን እንደ አካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ እየተላበሱ ኖረዋል። በሌላ ጊዜም የተጣለባቸውን የባህል ማዕቀብና ሁለንተናዊ ጭቆና በመሳሪያ ታግለዋል። በሰላማዊ የትግል ስልትም ሁኔታዎችን ለመቀየር ተንቀሳቅሰዋል።

የዛሬው ሙስሊም ኢትዮጵያዊ ከትናንቱ ሙስሊም የሚለይበት ባህሪያቶች ይኖሩታል። ባህላዊ ለውጥ */Cultural Transformation/* የሚነበቡባቸው ገፅታዎች ይስተዋሉበታል። ባህላዊ ንቃት */Cultural Awareness/* የብዙሃን ባህልና መለያ */Diversity and Pluralism/* አንድ መገለጫ በመሆኑ የሙስሊሙ ማህበረሰብ ኃይማኖታዊ ለውጥ ሌላውን ወገን ማስደንገጥ የለበትም። ከፅንፈኝነት ሊመደብም ሆነ በዚያ መልኩ መታየት አይኖርበትም። የሙስሊሙ ሃያማኖታዊ ባህል ለውጥና ዕድገት ከዕምነቱ መሠረታዊ መመሪያዎችና ሕግጋት አፈንግጦ ሕገ-መንግስታዊ ስርዓቱንም እስካላፋለሰ ድረስ ሊያስጨንቀን አይገባም። አላስፈላጊና ከሸሪዓችን ውጭ የሆኑ አካሄዶች ግን ሙስሊም ያልሆነው ወገን ብቻ ስጋቶች አይደሉም። የሁላችንም የጋራ ስጋቶችና ኃላፊነቶች ናቸው።

ሆኖም ግን ሙስሊሙ እምነቱን ለመተግበር መንቀሳቀሱ፣ እንደማንኛውም የሀገሪቱ ዜጋ በሀገሩ ጉዳይ ላይ ለመሳተፍ የሚያደርገውን ጥረት መቀበል ያቃታቸውና የሀገራችን እውነተኛ ገፅታ እንዳይንጸባረቅ የሚፈልጉ አካላትና ኃይሎች ሀገራችንን ወደማይፈለግ አቅጣጭ እንድታመራ እያደረጓት ነው። ሁኔታውን ለማረጋጋትም ሆነ ለወንጀለኞች ፍትህን ለመስጠት መንግስት የወሰደው እርምጃ የሚደነቅ ቢሆንም እስካሁን ህብረተሰቡን አርኪ ሆኖ ግን አልተገኘም፤ ወንጀሎችንም ማስቆም አልቻለም።





በኢትዮጵያ ህዝቦች የፓለቲካ ታሪክ ዉስጥ ኃይማኖት ከፍተኛ ሚና ነበረው። ከ700 አመታት በላይ የሀገሪቱ ገዥዎች አንድን እምነት ማዕከል ያደረገ ስርዓት በሀገሪቱ አካሂደዋል። በአሁኑ ሰዓት መንግስትና ኃይማኖት የተለያዩ ቢሆኑምና አንዱ በሌላው ውስጥ ጣልቃ መግባት እንደሌለበት ሕገ-መንግስቱ ቢደነግግም አንዱ ባንዱ ላይ ሊኖረው የሚችለው ተፅዕኖ ግን ሊካድ ወይም ሊዘነጋ አይገባዉም። ዜጎች በሕገ-መንግስቱ ከተቀመጠው የኃይማኖት እኩልነት ተጠቃሚ ለመሆን በሚንቀሳቀሱበት ወቅት የታሪክ ቁርሾ ሊነሳ ይችላል። እስካሁን ያየናቸው ኃይማኖትን መሰረት ያደረጉ ግጭቶችም ከዚሁ የሚመነጩ ናቸው ብለን እናምናለን።

ታሪካዊ መሰረት ሊኖረው የሚችል ወንጀል ግለሰቦችን በመቅጣት ብቻ ሊገታ የሚችል አይመስለንም። እስካሁን የተወሰዱ እርምጃዎች ወንጀሎችን ማቆምም ሆነ ህብረተሰቡን ማርካት ያልቻሉት በዚህ ምክኒያት ነው የሚል እምነት አለን። ወንጀለኛን ለፍርድ ከማቅረብና አስፈላጊውንም እርምጃ ከመዉሰድ በተጨማሪ ግጭቶችንና ወንጀሎችን አስቀድሞ ማምከንና መከላከል እጅግ አስፈላጊ ነው። ይህን ለማድረግ ህብረተሰቡ ስለመቻቻልና መከባበር አስፈላጊነትና ጥቅም፤ ችግሮችንም በውይይት መፍታት የሚያስችሉ መድረኮች በተለያየ ደረጃ ያስፈልጋሉ። ከዚህም በተጨማሪ በተለያዩ የኃይማኖት ተቋማትና ድርጅቶች መካከል መቀራረብ ኖሮ የሚመሩትን ህብረተሰብ ለልማት ማስተባበር የሚያስችላቸው አሰራርና ደንብ አስፈላጊ ነው። የኃይማኖት መሪ ድርጅቶችን የሚያቀራርብና በመካከላቸው ሊኖሩ የሚችሉ ችግሮችንም በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት የሚረዳ ገለልተኛ የሆነ አካል መኖር የግድ ይላል። ይህ አካል በተለያዩ ኃይማኖቶች መካከል የመቻቻል እና አብሮ የመኖር ባህል *(Culture of Tolerance and Co-existence)* እንዲዳብር፣ ኃይማኖታዊ ይዞታ ያላቸው ችግሮች ከመከሰታቸው በፊት ሊቀርፍ፤ ከተከሰቱም የመነሻ ምክንያታቸውን በማጣራት ለህብረተሰቡ ተአመኔታ ያለውና ትክክለኛ መረጃ ሊያቀርብ፣ እንደዚሁም ለመሰል ክስተቶች ዘላቂ መፍትሔ ሊያመነጭ ይችላል። ሀገራችን ያላትን ታሪካዊ ቦታ በተገቢው መልኩ በማቅረብ ከጎረቤት ሀገሮችና ከአለም ህብረተሰብ ጋር ሰላማዊ ግንኙነትን ለመፍጠር የሚያበረክተውም ሚና ቀላል አይደለም።

ክርስትናና እስልምና በኢትዮጵያ ውስጥ ተፎካካሪ ሳይሆኑ ተመጋጋቢ ሆነው መቀጠል ያለባቸው መሆኑን እናምናለን። እስላም የክርስትና ተቃራኒና ጠላት አይደለም። ክርስትናም እንደዚሁ። እነዚህ ሁለት እምነቶች አይጥና ድመት ሆነው የሚኖሩበት ምንም ምክንያት የለም። የአንዱ እድገት የሌላው ውድቀትም ነው ብለንም አናምንም። ያም ሆኖ ያሉ ችግሮች ልዩ ትኩረትን ይሻሉ፣ አግባብ ያለዉም የግጭት አስተዳደር ባህል */Conflict Management/* መከተል ያስፈልጋል። ይህ መጠነ ሰፊና ለአገራችን ሰላም፣ ለህዝባችን እድገትና ብልፅግና መሰረት የሆነ ኃላፊነት ለመወጣት በከፍተኛ ደረጃ የተዋቀረና የተደራጀ አሰራር አስፈላጊ ነው። ከዚህም በመነሳት መንግስት በሁሉም ሀይማኖቶች ዘንድ ተአመኔታ የሚኖረው የኃይማኖት ጉዳዮችን በሚኒስትር ደረጃ እንዲያቋቁም ሀሳብ እናቀርባለን።

# ማጠቃለያ

ቀደም ብለን በዝርዝር ላቀረብናቸው አንገብጋቢና ቁልፍ ጥያቄዎች የተከበሩ ጠቅላይ ሚኒስትር በጎ ምላሽ እንደሚሰጡን ተስፋችን የላቀ ነው። ከጥያቄዎቻችን መካከልም ለሚከተሉት ነጥቦች ተቀዳሚ ትኩረት እንዲሰጡልን በአክብሮት እንጠይቃለን።

- ***የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት በአዲስ እና በተጠና አወቃቀር ተቋቁሞ ለሀገሪቱ መንፈሳዊና ማህበራዊ ልማት ተጨባጭ አስተዋፅዖ የሚያደርግ ድርጅት እንዲሆን፤***

- ***የሀገራችንን እስላማዊ ታሪካዊና ባህላዊ መስህቦችን*** *(Ethiopian Islamic Historic and Cultural Heritages)* ***የሚያሰባስብ እና የሚጠብቅ ብሔራዊ እስላማዊ ሙዚየም*** *(National Islamic Museum)*፤ ***እንደዚሁም የጥናት፣ የምርምርና የማሰልጠኛ ማዕከል*** *(Center for Islamic Research and Training)* ***እንዲቋቋም።***

በመጨረሻም ያቀረብናቸውን ጥያቄዎቻችንን የሚከታተልና ከጠቅላይ ሚኒስትሩም ጋር ያለን ግንኙነት የተቀላጠፈ ሆኖ ቀጣይነት እንዲኖረው በማድረግ በኩል የሚረዳ አካል በአገር ቤት እንድናቋቁም፤ በጠቅላይ ሚኒስትሩ በኩልም እውቅና እንዲሰጥልን እንጠይቃለን።

እኛን ለማነጋገር እና ባሉን ችግሮች ላይ ለመወያየት መልካም ፈቃድዎ በመሆኑ፤ ወደፊትም ለሚደረግልን ማንኛውም ትብብር በኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ስም ምስጋናችንን በድጋሜ እናቀርባለን።